ዐቃቤ ህግ ክሱን የማስረዳት ሸክም ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም ስለሚባልበት አግባብ ፦

ያልታተመ የሰበር ውሳኔ ቅጽ 6 የሰ.መ.ቁ 212309 ተመልከቱ

በመሠረቱ በወንጀል ጉዳይ የሚሰጥ ውሳኔ በተከሳሹ ነጻነት ወይም ሕይወት ላይ የሚሰጥ ውሳኔ በመሆኑ በተከሳሹ ላይ የሚቀርበው ክስ ተከሳሹ የወንጀሉን ድርጊት ስለመፈፀሙ ብቻ ሣይሆን ወንጀሉ የተፈፀመበትን ጊዜ፤ወንጀሉ እንዴት እንደተፈፀመና ወንጀሉ በማን እንደተፈፀመ በዝርዝር መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግም በሚያቀርበው ማሥረጃ በክስ አቤቱታው ላይ የተገለፀው የወንጀል ድርጊት የተፈጸመ ስለመሆኑ እና የወንጀል ድርጊቱን ፈጻሚ ማንነት በትክክል ለይቶ ማሳየት እና በቂ እና አሳማኝ ሊባል በሚችል ሁኔታ የማስረዳት ሸክም (Burden of proof)እንዳለበት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 111፤ 141 እና 149 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ዓቃቤሕግ ክሱን የማስረዳት ሸክሙን ተወጥቷል የሚባለውም ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ይዘት እርስ በእርሳቸው የሚፋለሱ ፍሬጉዳዮችን ያልያዙ፤ወጥነት ያላቸው ተደጋጋፊ እና ተመሣሣይ ጉዳይ ማሥረዳት የሚችሉ እና ተዓማኒነት ያላቸው ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ፍ/ቤቱ ተከሳሹ እንዲከላከል ብይን ሊሰጥ የሚችለውም ዓቃቤሕግ ባቀረባቸው ማሥረጃዎች ተከሳሹ ወንጀል መፈፀሙን እና ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በተከሳሹ መፈፀሙ በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ያስረዳ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 (2)እና(4)፤57፤58(1) እና ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 እና 142 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ክስ አመልካች ሟችን ለመግደል ያነሳሳውን ምክንያት ያልጠቀሰ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዓቃቤሕግ ክሱን ለማስረዳት በፍርድ ቤቱ ቀርበው ከተሰሙት ምስክሮች ውስጥ 1ኛ ምስክር በእለቱ ከ2ኛ አመልካች እና ፍሬው ከተባለ ሰው ጋር ሲጠጡ እንደነበር ምስክሩ ትቶአቸው ቀድሞ እንደሄደ፤ በማግስቱ 2ኛ አመልካች ደውሎ ከእኛ ጋር የነበረችው ሴት ሰው ገድሎታል ፖሊሶች ከያዙህ አትንዘባዘብ እንዳለው በመቀጠልም ወደ አዲስ አበባ እንሂድ ስለእኔ ከተናገርክ እገድልሃለሁ እንዳለው የመሰከረ ነው፤ 2ኛ ምስክር ጩኸት ሰምቼ ስወጣ ድምጽ አለ ከፍ ተደርጎ የተከፈተ የሚዘፍነ ሞባይልም አለ ሟች የተገደለችበት ቦታ መብራት ነበር ደብዳቢዎቹን ግን ከሩቅ ቦታ ስለነበር አላየኋቸውም በማለት የመሰከረች ነች፤ 3ኛ፤ 4ኛ እና 5ኛ ምስክሮች ደግሞ ጨሌ በቤርጎ ቁጥር 2 ተንጠልጥሎ ያገኙ እና ጨሌውም የሟች መሆኑን በመግለጽ ከመመስከራቸው በቀር በእርግጥም በክሱ በተገለጸው ሁኔታ አመልካቾች የግድያ ወንጀሉን ሲፈጽሙ አይተናል በማለት የተሰጠ የምስክርነት ቃል የለም፡፡ ይህም ከመነሻውም ቢሆን ዓቃቤሕግ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ በቂ እና አሳማኝ ሊባል በሚችል ማስረጃ ያላስረዳ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

paul.k (judge)

Last modified: 8:37 am